# የአገልግሎት ክፍያ ቅናሾች




## UTILITY DISCOUNT PROGRAMS (UDP) (የአገልግሎት ቅናሽ ፕሮግራሞች)

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ነዋሪዎች **የጋዝ፣ ውሀ፣ ኤሌክትሪክ**፣ እና **ስልክ** አገልግሎት ክፍያቸውን እንዲከፍሉ ለመርዳት ፕሮግራሞችን ያቀርባል።

**የፕሮግራም መግለጫዎች፣**

### Residential Essential Service (RES) (የመኖሪያ መሰረታዊ አገልግሎት)

ብቁ የሆኑ በግዛቱ ውስጥ ያሉ የWashington (ዋሺንግተን) ጋዝ ደምበኞች በክረምት ወቅት ከኖቬምበር እስከ ኤፕሪል ድረስ ባለው የሙቀት ጊዜ ለሚጠቀሙት የተፈጥሮ ጋዝ ከፊሉን ቅናሽ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

በRES ለመሳተፍ፣ የዲስትሪክት ነዋሪዎች የተፈጥሮ ጋዝን እንደ ቀዳሚ የሙቀት ምንጭ መጠቀም አለባቸው። ለRES ብቁ የሆኑ ደምበኞች ከአጠቃላይ ክፍያ በግምት 46% የሆነ ቅናሽ ያገኛሉ።

### Residential Aid Discount (RAD) (የመኖሪያ እርዳታ ቅናሽ)

በዲስትሪክቱ ውስጥ ብቁ የሆኑ የፔፕሲኮ (Pepco) ደንበኞች ለመኖሪያ እርዳታ ብድር (RAC) ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ብድር በፔፕሲኮ ማቅረቢያ ክፍያዎች እና ግብሮች ላይ ቅናሽ ይሰጣል።

በየአመቱ $300-475 የመቆጠብ አቅም።

### Customer Assistance Program (CAP) (የደምበኛ ድጋፍ ፕሮግራም)

በግዛቱ ውስጥ ያሉ ብቁ የሆኑ የመኖሪያ የDC (ዲሲ) ውሀ ደምበኞች በእያንዳንዱ ወር ለተጠቀሙበት እስከ 400 ኩዩቢክ ጫማ (4ccf ወይም በግምት 3,000ጋሎን) ውሀ እና የሽንት ቤት ውሀ አገልግሎቶች ድረስ ቅናሽ ለማግኘት ብቁ ሊሆን ይችላል።

ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች ከወርሀዊ የClean Rivers Impervious Surface Area Charge (CRIAC) (የንጹህ ወንዞች የኢአስራጊ ከባቢ ቦታ ክፍያ) ሀምሳ ፐርሰንት (50%) ተጨማሪ ብድር ያገኛሉ።

በየአመቱ ከ$500.00 በላይ ቅናሽ ሊኖር ይችላል።

### Lifeline Services (የላይፍላይን አገልግሎቶች)

Economy II Service (ኢኮኖሚ II ሰርቪስ)፣ “Voice Lifeline” (ቮይስ ላይፍላይን) ተብሎ በተጨማሪ የሚታወቀው በVerizon (ቬሪዞን) የሚሰጥ የድጋፍ ፕሮግራም ነው። ብቁ የሆኑ የDC (ዲሲ) ደምበኞች ቅናሽ የቤት የአገር ውስጥ የስልክ አገልግሎት ይሰጣል። Voice Lifeline Service (ቮይስ ላይፍላይን አገልግሎት) እድሜያቸው ከ65 አመት በታች ለሆኑ በወር በ$3.00፣ እና እድሜያቸው 65 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ አዋቂዎች በወር በ$1.00 ይቀርባል።

የ Lifeline ማመልከቻ ለማግኘት፣ **lifelinesupport.org**
ይጎብኙ ወይም ወደ 1-800-234-9473 ይደውሉ።

**እባክዎ ስለ ምዝገባ ሂደት፣ የገቢ ብቁነት፣ እና የሰነድ መስፈርቶችን ለማየት ጀርባውን ይመልከቱ።**

Washington Gas
pepco AN EXELON COMPANY
dc water is life
verizon
OPC-DC Office of the People's Counsel
PUBLIC SERVICE COMMISSION District of Columbia
DEPARTMENT OF ENERGY & ENVIRONMENT
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የአገልግሎት ክፍያ ቅናሾች

## የምዝገባ ሂደት እና የገቢ ብቁነት መስፈርቶች

## UTILITY DISCOUNT PROGRAMS (UDP) (የአገልግሎት ቅናሽ ፕሮግራሞች)




### CAP፣ RAD፣ RES አዲስ አመልካቾች፣

1. በ doee.dc.gov/udp ኦንላይን ያመልክቱ

2. ለበለጠ መረጃ ወደ 311 ይደውሉ።

### አሁን ያሉ የUDP ተሳታፊዎች

1. DOEE አሁን ላሉ የ CAP፣ RAD፣ እና RES ተሳታፊዎች የማመልከቻ መልእክት በፖስታ ይልክላቸዋል። ተሳታፊዎች ምላሽ ለመስጠት 30 ቀናት አላቸው።

2. የእርስዎን የCAP፣ RAD፣ እና/ወይም RES ማመልከቻ ሁኔታ ለማየት፣ ወደ 311 ይደውሉ።

### አዲስ የLifeline (ላይፍላይን) ተሳታፊዎች፣

የLifeline (ላይፍላይን) የገቢ ብቃት መስፈርቶች ከላይ ከተገለጹት ይለያሉ። Medicaid፤ ተጨማሪ የምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (“SNAP”)፤ ተጨማሪ የዋስትና ገቢ (“SSI”)፤ የፌደራል የህዝብ መኖሪያ ቤት ድጋፍ፤ የተረፉ የቀድሞ ወታደሮች የኗሪዎች የጡረታ ጥቅማጥቅም ማግኘት አለብዎ፤ ወይም ከፌደራል የድህነት ደረጃ ከ135% ያነሰ ገቢ ሊኖርዎ ይገባል።

ለበለጠ መረጃ እና ለማመልከት፣ lifelinesupport.org ይጎብኙ ወይም ወደ 1-800-234-9473 ይደውሉ።

### የገቢ ብቃት መስፈርቶች

FY 2023 (ኦክቶበር 1፣ 2022 - ሴፕቴምበር 30፣ 2023)

| # በቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች | ከፍተኛ አመታዊ ገቢ |
|---|---|
| 1 | $79,700 |
| 2 | $91,100 |
| 3 | $102,500 |
| 4 | $113,850 |
| 5 | $125,250 |
| 6 | $136,650 |
| 7 | $148,050 |
| 8 | $159,400 |

### የሚያስፈልጉ ሰነዶች

- የእርስዎ በጣም የቅርብ ጊዜ የአገልግሎት ክፍያዎች
- በመንግስት-የተሰጠ ፎቶ ያለው መታወቂያ
- በቤትዎ ውስጥ ገቢ የሚያገኙ የእያንዳንዱ ሰው የገቢ ማረጋገጫ
- በቤትዎ ውስጥ ያሉት የእያንዳንዱ የማህበራዊ ዋስትና ካርዶች

ስለ UDP የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ወደ **311** ይደውሉ ወይም doee.dc.gov ይጎብኙ

Video Relay Services (VRS) (የቪዲዮ ሪሌይ አገልግሎቶች) ተጠቃሚዎች ወደ 202-727-1000 መደወል አለባቸው